# የቴዲ አፍሮ ወንጀል ተረጋገጠ

ማንም ምን ይበል አዎን ቴዲ ገዳይ ነው። ቴዲ እንኳን ቆሞ የሚሄድን ክፉት ይቅርና የተኛን መሰሪነት ሊደፈጥጥ እንደሚችል ሺህ ምስክሮች ማቅረብ ይቻላል። የኢትዮጵያ ሕዝብም ይህንኑ ስላረጋገጠ ጉዳዩን በአደባባይ ከተነጋገረበት ቆየ «... *አንተ የሌለህበት አዲስ ዘመን አሮጌ ነው ኢያለ* ....»። ቴዲ ብዙ ገድሏል። ክፉትን አላዘነለትም፣ ጥላቻን በሚዘገንን መልኩ ገድሏል፣ መነጣጠልንና መበታተንን አቁስሎአል። ጎጠኛነትን ቂመኛነትን አደባባይ ረሽኖአል። እጅግ በጣም ወገንተኛ ነው ለፍቅር ያደላል። ይህ ጠበቃና ዳኛን አይሻምና እኒህ በሙሉ በወራሪዎቹ በወያኔዎች አገዛዝ ወንጀሎች ናቸው። ስለዚህ የቴዲ ወንጀል የሀገርና የወገን ፍቅር ነው። በዚህ እጅጉን ስለተለከፈ የፍቅር አዙሪት መልሶ መላልሶ ወደ ሀገሩ ያመጣዋል። እንደሌሎቹ ከሀገር እንደወጣ አልቀረም። የጀግንነት ማስተንፈሻ በሆነው የስደት መንገድ እንዲፈተለክ ቀዳዳ አበጅተው ከፍቅር ሊያሸሹት አልተቻላቸውም። ስለዚህም በነርሱ ደንብ ፈጣጣ ወንጀለኛ ነው። አንዳንድ ገጣሚዎች «... *ኢትዮጵያ ቃሊቲ ቃሊቲም ኢትዮጵያ፣ ምን ልዩነት አለው እዚህ ሆንን እዚያ።* ....» ብለው ስንኝ ቋጥረውለታል። የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባኛል ያሉ ሁሉ የቴዲን ስም ከፍ አድርገው አሰምተዋል። ይሁን እንጂ ትልቁ እስር ቤት ኢትዮጵያ ያለን ሰዎች ትንሿ እስር ቤት ቃሊቲ ካለው የምንለየው እጅግ በትንሹ ነው።

ይህን ወንጀለኛነት እያወቅሁ ለምን እንባዬ በጉንጬ ለመውረድ እንደቻለ ለማወቅ አልቻልኩም። ሲያለቅስ ለሚኖር ሕዝብ ስለእንባ አይነግሩትም እንጂ የፍርድ ቤቱን ነገር እያነበብኩ ለቴዲ ሳይሆን ለራሴም ማልቀሴ ነበር። ምክንያቱም እፍኝ የማይሞሉ ወራሪዎች ይህን ያህል ሲያደርጉ ምን አይነት አፍዝ አደንግዝ ውስጥ እንደሆንን መልሼ ማስታወስ በመገደዴ ነው ማለት ነው። የዛሬው ገዢ የወያኔዎች ቡድን የትግራይ ልጆችን እያሳረደ ገና ከመነሻው ራሱን ከፍ ያደረገው በሀሰት ክስ የሰለጠነ ስለነበር ነው። በዚህ የስራ ልምዱ የተካነ ነውና አዲስ የሚባል ነገር በቴዲ ላይ አላየሁም። ነገር ግን ወያኔዎችን እንደ ኢትዮጵያዊ እንድንፈርጃቸው ምን አጃጃለን የሚል ቁጭት በውስጤ ተነሳ። ምናልባት ትንተናችንና አፈራረጃችን ያው እኛን ስለሚመስሉና እንደ ኮሶ ከተጣቡት ከትግራይ ሕዝብ ጉያ ስለወጡ ብቻ እንጂ አንዲትም ስፍራ፣ አንድም ቀን ለኢትዮጵያ ቀና ነገር መስራት ቀርቶ ቀና ነገር እንኳ ሲናገሩ የተደመጠበት የለም። እና እንዴት ሆኖ ነው ወራሪዎች፣ ነጣቂዎች፣ ቅጥረኞችና ነብሰ ገዳዮችን መንግስት አድርገን ፍትህ ከነርሱ የምንጠብቀው? ገና ከወጣትነታቸው ጀምሮ እንደ ፓራሳይት የተጣቡትን የትግራይ ሕዝብ ደም እየመጠጡ፣ ትምህርት ቤቱን፣ ድልድዩን ሆስፒታሉን እያፈረሱ የራሳቸውን ወገን፣ በጉያው የተሸከማቸውን ወገን አሳር ያሳዩ መሆናቸውን እንዴት ልንረሳው ይቻለናል? የትግራይን ወጣት ገበሬዎች በመሰሪነት ለእርድ ያሰማሩ መሆናቸውን እንዴት እዘነጋለሁ። ለፖለቲካ ድል ሲባል ወገኔ የሚሉትን ሕዝብ ገበያ መሀል እያስገደሉ ፊልም የሚቀርጹ መሆናቸው የአደባባይ ሚስጥር አይደለም? በመሀል ሀገር እንደ ወገን እንደ ወዳጅ እንደተገፉ ሰው እያኮረፉና ሲመቻቸው አገር እየናዱ « .... *ውስጣቸው ሆነን አፈራረስናቸው* .....» የሚሉንን እንደዋዛ በመመልከታችን ነው ይህ ሁሉ ክፉት የሚፈጸምብን። አልፈው ተርፈው እኒህ ወራሪዎች ዛሬም የሚነግሩን ምንድን ነው?

አዎ ወያኔ አንድ ነገር ነው እያለን ነው ያለው። አንድ ነገር ብቻ!! ምናባታችሁ ትሆናላችሁ እናንተ ግብዞች፣ እናንተ እርስ በእርስ እንኳን ተነጋግራችሁ ወደ ቁም ነገር የማትመጡ ልፍስፍሶች፣ እናንተ ፈሪዎች ከመደናበርና እርስ በእርስ ከመቋሰል በቀር ምን እርባና አላችሁ? ያሻንን ብናደርጋችሁ ምን ልታመጡ ነው ነው የሚሉት። ምንም በእርግጥም ምንም ልናመጣ የማንችል መሆናችንን በተደጋጋሚ አስመስክረናል። ምክንያቱም ተምታቶብናላ! ወያኔን ልንገርፍበት በሚገባን አርጩሜ እርስ በእርስ እንዣለጣለን። ወያኔን መንግስት አድርገን ፍትህ እንጠብቃለና፣ ወያኔዎች ቋንቋችንን ስለሚናገሩ አገር በቀል ሆነው በትግራይ ልጆች ከለላ ስለመጡ እንደ ወራሪ ሳይሆን እንደ አምባገነን መንግስት አድርገን ተቀብለን እየኖርን ነዋ። የጎጥ መሪዎች ትናንሽ ንጉስ ለመሆን ከወራሪ ላይ ተለጥፈው ሕዝባቸውን ያስፈጃሉ። የትኛውም የኢትዮጵያ የፖለቲካ እንቅስቃሴን አንድ ሊያደርግ የሚገባው የሀገር ህልውና ጉዳይ መሆን ሲገባው አገር ያለን ይመስል ተባድነን እንናቆራለን። ይህ ካላሳዘነኝ፣ ይህ ካላንገበገበኝ፣ አገሬ ስትሞት ካላለቀስኩኝ እንባ ለምን? ለቅሶስ ለመቼ? ይህ ነው መንፈሴን የረበሸው፣ ይህ ነው ያስቆጣኝ። «በጥፍሬ ቧጥጬም ይሁን በጥርሴ ነክሼ ከጫንቃዬ ላይ ወራሪዎችን ላስወግድ ይገባል» ያለች ወጣት ድምጽ እንደትውስታ ሰውነቴን ወረረኝ። እናም ወያኔን ካላስወገድሁ እንኳን እንደ ቴዲ አደባባይ ፍቅርን መስበክ፣ ለአንድነት መዘመር ይቅርና ሚስቴና ልጆቼንም እወዳችኋለሁ ለማለት መፍራት ግዴ ሊሆን ነው ማለት ነው። በዚህ አይነት እየኖርኩኝ ሀገር አለኝ ለማለት እንዴት ይቻለኛል? አንዲት ወጣት «... እናቴን ሁለቴ አልገድላትም... የገደላት አጋዚ ነው...» ብላ የጮኸችው ሁሉ በደጋሚ ታወሰኝና መንፈሴ ታወከ። በዐለማችን ላይ እንደ ኢትዮጵያ ሕዝቡን የፊጥኝ አድድስሮ ለሌሎች ጉልበተኞች ሎሌ ሆኖ ሕዝቡን የሚያስፈጅ መንግስት በየትኛውም ክፍለ ዐለም የለም። ከወራሪዎች ራሳችንን ነጻ እናውጣ! የጎጥ ከለላ፣ የድርጅት ጥላ ሳይሆን የሀገር ህልውና ከሁሉም በላይ ከፍ ሊል ይገባዋል የሚል የህብረት ጥሪ ነው ከያቅጣጫው ሊሰማ የሚገባው። የዱላ ምርጫ የምናደርግበት ምቾት ላይ አይደለንም። በክትክታም ይሁን በወይራ ወይም በሰላማዊም ይሁን ወያኔ ሕገወጥ በሚለው መንገድ ይሁን ተጋግዘን ነጻ ልንወጣ ይገባናል።

ጀግኖቻችንን እየናቅን የጀግና ያለህ እንላለን፣ በፍቅር በአንድነት በፈጣሪ ፍራቻ የተጠመቀ ወጣት ልጅ ስለፍቅር ስለዘመረ እንዲህ ያለ ክፉት ሲፈጸምበት ወያኔን ከጣልያን ወራሪ አሳንሰን ለመመልከት እንዴት ይቻለናል? እስኪ ወያኔ እንደ ኢትዮጵያ መንግስት ለኢትዮጵያ

ይህን አደረገ ብሎ የሚነገር ነገር አለ? የንቀታቸው መጨረሻ ጎንደርን ለሱዳን፣ ደብረዘይትን ለጅቡቲ አዋሳን ለሳውዲ አረብያ ሸጡ። የኢትዮጵያ ሕዝብ እየተራብ ለአረብ ቱጃሮች የእርሻ መሬት ይሰጣሉ። ኢትዮጵያውያን ነገሮች አልገቡንም ወይስ ተስፋ ቆርጠናል? ምንድን ነው የምንፈልገው? ዘወትር ኢትዮጵያውያን በየስብሰባው ሀገራችን ቅኝ ተገዝታ የማታውቅ ሀገር ነች እንላለን የአያቶቻችንን ታሪክ ለመንገር። ነገር ግን አሁን ዛሬ በወራሪ ተገዝተን አገራችንን እንዳሻቸው በሚሸነሽኑ፣ በሚሸጡ እዚህ ግባ የማይባሉ አውሬዎች መንጋጋ ተነክሰን ታሪክ ብናወራ ምን እርባና አለው? አያቶቻችን ጀግንነታቸውን አስመስክረው አልፈዋል። እኛ ግን ፈሪዎች ነን፣ ተጠራጣሪዎች ነን። አንድ ቋንቋ እየተናገርን አንግባባም። ይህ እስከመቼ ሊሆን ይቻለዋል?

በቴዲ አፍሮ ላይ የሚደርሰው ነገር አንድ ነገር ያሳስበናል። አንድነታችንን የምናጠናክርበት፣ ሕብረታችንን ቃል ኪዳናችንን የምናድስበት ሊሆን ይገባል። ኢትዮጵያ ተደፍራለች፣ ሕዝብዋ የፊጥኝ ታስሮ በወራሪዎች እየተጋዘ፣ እየታሰረና እየተገደለ ነው። ይህን እየተመለከትን ጥቂት ሆዳሞች ፓርላማውን እያሟሟቁ ኢትዮጵያዊ ገጽታ የሚሰጡት ይህን ጨቋኝ ቂመኛና ማፊያ የገዢ ቡድን ከትግራይ ሕዝብ ጉያ እንዳይሸሸግ ለማድረግ መነሳት አለብን። የታሰረው ቴዲ አፍሮ ሳይሆን ኢትዮጵያና ሕዝብዋ ናቸው። ፈራጆቹ ነገ የቆሙበት መሬት የሚከዳቸው ምንደኞችና ሰብዓዊ ክብራቸውን በሆዳቸው የለወጡ የትውልድ ዝቃጮች ናቸው። የኢትዮጵያ ጀግኖች በተፍረከረኩና መንገድ ለጊዜው በጠፋቸው ሰዎች ምክንያት ሊዘናጉ አይገባም። ዋናው የኢትዮጵያ ጠላት የሆነውን የወያኔ የወራሪ ኃይል ከጫንቃችን ለማውረድ ዛሬ ቃል የምንገባበት ሊሆን ይገባዋል። ጣት የምንጠነቋቆልበት ሳይሆን የአቅማችንን በኢትዮጵያዊ ጨዋነት የምናበረክትበትን ቃልኪዳን የምናድስበት ሊሆን ይገባል። እኛ ጠንካራ አዋቂና አስተዋይ ከሆንን ደካማ ድርጅቶች ጠንካራ ይሆናሉ። ሁላችንም አዋቂና ከሳሾች ግን ቅንጣትም አስተዋጽኦ የማናደርግ ከሆነ አልተናገርነውም እንጂ ሽንፈታችንን በጸጋ ተቀብለናልና ዝም እንበል። ነገር ግን እኔም እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ የዜጋ ድርሻ አለብኝ ኢትዮጵያ አላበቃላትም የምንል ከሆነ ዛሬ ነገ ሳንል የድርሻችንን እናበርክት። ድርጅቶች የሕዝብን ፍላጎትና ስሜት ካልተረዱ በራሳቸው ይጠፋሉና ከአሉባልታ ነጻ ሆነን ሀሳባችንን እውቀታችንን ስሜታችንን ወደ አንድ በማምጣት አገራችንን አንታደጋት።

ቴዲ በነጻነትና በፍቅር በልባችን ውስጥ ታላቅ ስፍራ ይዞ ይመላለሳል። የእስላም የክርስትያኑን ፍቅር ኃያልነት እያበሰረ እጅ ለእጅ እንድንያያዝና ከጫንቃችን ላይ የተቀመጠውን ወራሪ አሽቀንጥረን እንጥል ዘንድ ተስፋ አለን። ቴዲ በአካል ከመካከላችን እስኪገኝ ድረስ ኡ ኡታውን እያስታወስን አንከዳህም እያልነው አብረን ነን። በእስር፣ በስደት ተበታትነን ነው ያለነውና በቃሊቲ አጥር ውስጥና በውጭ ያለው ሁኔታ አንድ ነው። ሁላችንም ከዚህ እስር እንድንፈታ በጋራ አንድ ሆነን እንነሳ!!!! እያንዳንዳችን በነብስ ወከፍ የምናበረክተው ሲደመር ነው ሀገር አቀፍ ውጤት የሚያመጣውና ሁላችንም የድርሻችንን እናበርክት። ቀዳሚው የኢትዮጵያ ህልውና ነውና ለዚህ ቃልኪዳናችንን እናድስ።

ዳኛቸው ቢያድግልኝ

biyadegelgne@hotmail.com